ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ
D.N Solomon Yohannes

መቅድመ ኵሉ አፍቅሮ ለእግዚአብሔር
አምላክከ ።

ትእዛዙ ለእግዚአብሔር ብሩህ
ወያበርህ አዕይንተ ።

# ስለ ክርስቲያን ሃይማኖትና ምግባር ከሊ.ቀ ሊ.ቃ ውንት ገብረ አብ (አባ ፊልጶስ) ኦርቶዶክሳዊ

የካቲት ፲፰ ቀን ፲፱፻፵፮ ዓመተ ምሕረት ።
ሁለተኛ የተጻፈ ያምክር ቃል ።

በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ ፲፰ ፯ ፵፮ ቀ ፲፱፻፯ መ ፳፪

www.ethiopianorthodox.org



ብፁዕ ፡ አባ ፡ ባስልዮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

www.ethiopianorthodox.org

ዲያቆን ሰሎሞን
D.N Solomon Yohannes
0911860113
0111271609



ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ፊልጶስ ።



www.ethiopianorthodox.org

## ማስታወቂያ ።

በዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ መታሰቢያ ፡ ቤት ፡ ኃላፊ ፡ ሆኜ፡ ስሠራ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ በ፲፱፻፳፮ ዓ ም ፡ በታኅሣሥ ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ የእመቤታችንን ፡ በዓል ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ይህ ችን ፡ የሃይማኖትና ፡ የምግባር ፡ መግለጫ ፡ ትንሽ ፡ መጽሐፍ ፡ ሃይማኖትን ፡ ለማጽናት ፡ ምግባርን ፡ ለማስፋፋት ፡ ምእመናንን፣ ትረዳለች ፡ የሰባክያንንም ፡ ልቡና ፡ ታበረታታለች ፡ በማለት ፡ አሳትሜያት ፡ ነበረ ።

ከሰባክያንም፡ከምእመናንም፡ወገን፡ያንጊዜ፡ የመጽሐፏን፡ ጥቅም ፡ የተረዱት ፡ ሰዎች ፡ መላልሰው ፡ ስለጠየቁኝ ፡ በ፴፫ ዓ ፡ ም ፡ የካቲት ፡ ፳፬፡ ቀን ፡ ገንዘብ ፡ ከፍዬ ፡ ሁለተኛ፡ ማሳተሜን ፡ እየገለጥኩ ፡ መጻሕፍተ ፡ ሊቃውንትን ፡ ከብሉያትና ፡ ከሐዲሳት ፡ እያስማሙ ፡ ለሚሰብኩ ፡ ሰባክያን ፡ አበረክታለሁ ።

አባ ፊልጶስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን
ጳጳስ በኢየሩሳሌም ።

www.ethiopianorthodox.org

| ተራ ቁ | ማውጫ ። | ገጽ |
|---|---|---|
| ፩ | መቅድም ። | ፱ |
| ፪ | ስለ ፡ አዳም ፡ ተፈጥሮና ፡ ስለ ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋ ፡ ስለ ፡ ፈቃደ ፡ ነፍስ ፡ ጦርነት ። | ፲፩ |
| ፫ | ለሰው ፡ ሕግ ፡ ስለመሠራቱ ። | ፲፫ |
| ፬ | ፀሥሩ ፡ ቃላት ፡ ስለሚፈጸሙበትና ፡ ስለ ሚፈርሱበት ፡ ምክንያት ። | ፲፰ |
| ፭ | እመቤታችን ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ስለ መግባቷና ፡ ከዚያው ፡ ጌታን ፡ ስለመጽነሷ ። | ፳፯ |
| ፮ | ፲ቱ ፡ ቃላት ፡ በወንጌል ፡ ስለመጽናታቸው ፡ | ፳፱ |
| ፯ | ከሐዋርያት ፡ በኋላ ፡ የተነሡ ፡ ሊቃውንት ፡ ሥርዓተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ማከናወን ፡ የሚገባቸው ፡ ስለ ፡ መሆኑ ፡ | ፴፫ |
| ፰ | ጾም ፡ በወንጌል ፡ የታዘዘ ፡ ሕግ ፡ ስለመሆኑ ። | ፴፯ |
| ፱ | ሊቃውንት ፡ የሠሩትን ፡ ሥርዓት ፡ መቀበል ፡ የሚገባ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ። | ፴፱ |

## መቅድም ።

፲፱፻፷፯ ፡ ዓ.ም ታኅሣሥ ፡ ፫ ፡ ቀን ።

በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ቅዱስ ፡
በአካል ፡ ፫ ፡ ብለን ፡ ፩ ፡ ገጽ ፡ ከማለት ፡ ተጠብቀን ፡

፩ዱ አምላክ ። በባሕርይ ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ ብለን ፡ ፫አማልክት ፡ ከማለት ፡ ተጠብቀን ፤ ክቡር ፡ ዳዊት ፡ የሥጋ ዊን ፡ ነገር ፡ በተናገረበት ፡ አንቀጽ ፡ ልጅ ፡ ገርሮሽን ፡መል ሰሽ ፡ ስሚ ፡ ንጉሥ ፡ ባሕርይሽን ፡ ለተዋሕዶ ፡ መርጧልና ፡ ወገኖችሽንና ፡ ያባትሽን ፡ ወገን ፡ እርሺ ፡ ብሎ ፡ ስለሷ ፡ የተናገረው ፡ ትንቢት ፡ ሊፈጸም ፡ ከአዳምና ፡ ከሔዋን ፡ ተወልዳ ፡ ስንኳን ፡ በገቢርና ፡ በነቢብ ፤ በሐልዮ ፡ ስንኳ ፡ ስሕተት ፡ የሌለባት ፡ እመቤታችን ፡ በተወለደች ፡ በ፫ ፡ ዓመት ፡ ከናት ፡ ከአባቷ ፡ ተለይታ ፡ ምሳሌዋ ፡ ወደምት ሆን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ የገባችበትን ፡ ዕለት ፡ ለማክበር ፡ የተ ሰበሰባችሁ ፡ ምዕመናን ሆይ ፤ ክርስቲያን ፡ ከሆነ ፤ ሲበድ ሉት ፡ የሚታገስ ፡ ተበድሎም ፡ የሚክስ ፡ ኢየሱስ ፡ ክር ስቶስን ፡ አጋዥ ፡ ሳትሻ ፡ በድንግልና ፡ የወለደችልን ፡ ድንግል ፡ ማርያምን ፡ ከማክበርና ፡ ከመውደድ ፡ ምንም ፡ ልቡናው ፡ ተግ ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ባይኖር ፤ ይህ ፡ መሰብሰ ባችን ፡ በከንቱ ፡ እንዳይደለ ፡ ዋጋ ፡ ያለበት ፡ እንደሆነ ፡ ለማሳሰብ ፡ የተቻለንን ፡ ያህል ፡ ከሙሉ ፡ በክፍሉ ፡ ከብዙ ፡ በጥቂቱ ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ አወጣጥተን ፡ እንጽፉለ ንና ፡ ሕፀፃችንን ፡ ሳትመለከቱ ፡ ነቅታችሁ ፡ ተግታችሁ ፡ እንድትሰሙን ፡ እናማልዳችኋለን ።



www.ethiopianorthodox.org

ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ አወጣጥተን ፡ የምንናገረው
ንም ፡ ቃል ፡ በጽሕፈት ፡ ለመግለጽ ፡ ያተጋን ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ተገልጦም ፡ ቢሆን ፤ በወዳጆቹ ፡ በቅዱሳን ፡ አድሮም ፡
ቢሆን ፤ ሥራ ፡ የሠራባቸውን ፡ ዕለታት ፡ ሥራ ፡ ፈትተው ፡
በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተሰብስበው ፡ ማክበር ፡ ለምእመናን ፡
የግድ ፡ ሥርዓታቸው ፡ እንደሆነ ፤ መምህራንም ፡ በመከ
ከል ፡ ቆመው ፡ ምእመናን ፡ በሕገ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸን
ተው ፡ የሚኖሩበትን ፡ ምክር ፡ እዝናት ፡ እንዲያስተምሩ ፡
በግድ ፡ ሥርዓታቸው ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ከሐዋርያት ፡ ሲያ
ያዝ ፡ የመጣ ፡ ነው ። ግብ ፡ ፲፬ ፲፫ ፡ ፲፭ ፲፯ ።

ነገር ፡ ግን ፡ የተቻለንን ፡ ያህል ፡ ቃል ፡ ለቃል ፡ ተነ
ጋግረን ፡ ሳይጻፍ ፡ ቢቀር ፡ ስንኳንስ ፡ ሰማዕያኑ ፡ ፩ድ ፡ ጊዜ ፡
በሰሙት ፡ ቃል ፡ ነገሩን ፡ ተረድተውት ፡ ሥራ ፡ ሊሠሩብ
ትና ፡ መምህራኑም ፡ ቅሉ ፡ በቃል ፡ የተናገርነውን ፡ መል
ሰን ፡ በቃል ፡ እንናገረው ባልን ፡ ጊዜ ፡ ንግግራችን ፡ ሳይ
ለወጥ ፡ እንዳይቀር ፡ የታወቀ ፡ ነው ። የተጻፈ ፡ እንደሆነ ፡
ግን ፡ ቃሉ ፡ ጥቅም ፡ ያለበት ፡ ከሆነ ፡ እስከ ፡ ልጅ ፡ ልጅ ፡
ጥቅሙ ፡ ሳያቋርጥ ፡ ይኖራልና ፡ የሚነገረው ፡ የስብከት ፡
ቃል ፡ ሁሉ ፡ በጽሕፈት ፡ ቢሆን ፡ የተሻለ ፡ ስለመሰለን ፡ ነው ።

ምዕራፍ ፩

ስለ ፡ አዳም ፡ ተፈጥሮና ፡ ስለ ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋ ፡ ስለ ፡ ፈቃደ ፡
ነፍስ ፡ ጠርነት ።

፩ ፡ ዓለምን ፡ ከመፍጠሩ ፡ አስቀድሞ ፡ ባንድነት ፡ በ፫
ነት ፡ እየተሠለሰ ፡ እየተቀደሰ ፡ ያለችግር ፡ ነግሦ ፡ ይኖር ፡
የነበረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ግዳጅ ፡ ኖሮበት ፡ ግዳጅ ፡ ይፈ
ጸምልኛል ፡ ሳይል ፡ በቸርነቱ ፡ ብዛት ፡ ከለመኖር ፡ ወደ ፡
መኖር ፡ አምጥቶ ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ ፈጠረ ፡ ዘፍ ፡ ም ፩ ፡
ቍ ፡ ከንድ ፡ እስከ ፡ ፳ ።

፪ ፡ ፍጥረት ፡ በጀመረ ፡ በ፮ተኛውም ፡ ቀን ፡ አዳምን ፡
በመላእክት ፡ አምሳል ፡ ፈጥሮ ፡ በባሕርዩ ፡ ለሚገዛው ፡
ከሰማይ ፡ በታች ፡ ላለው ፡ ፍጥረት ፡ በጸጋ ፡ ገዥ ፡ አድ
ርጎ ፡ አነገሠው ።

፫ በመላእክት ፡ አምሳል ፡ ፈጠረውም ፡ ማለት ፡ እን
ደመላእክት ፡ ረቂቅ ፡ አድርጎ ፡ ከእሳትና ፡ ከነፋስ ፡ ብቻ ፡
ወይም ፡ እምነበ ፡ አልበ ፡ ፈጠረው ፡ ማለት ፡ አይደለም ።

፬ ፡ መላእክት ፡ ይህን ፡ ሥሩ ፡ ይህን ፡ አትሥሩ ፡ የሚል ፡
ሕግ ፡ ሳይጻፍላቸው ፡ በተፈጥሮ ፡ በተሰጣቸው ፡ እው
ቀት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፈርተው ፡ አምልኮቱን ፡ አጽ
ንተው ፡ ክፉና ፡ በጎ ፡ ለይተው ፡ ከክፉ ፡ ተጠብቀው ፡
በጎውን ፡ ሠርተው ፡ ስሙን ፡ እየቀደሱ ፡ ክብሩን ፡ እን
ዲወርሱ ፡ ዕብ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፲፬ ።

ሰውም ፡ ይህን ፡ ሥራ ፡ ይህን ፡ አትሥራ ፡ የሚል ፡
ሕግ ፡ ሳይጻፍለት   በሕገ ፡ ልቡና ፡ እግዚአብሔርን ፡

www.ethiopianorthodox.org

ፈርቶ ፡ አምልኮቱን ፡ አጽንቶ ፡ ክፉና ፡ በጎ ፡ ለይቶ ፡ ክፉውን ፡ ትቶ ፡ በጎውን ፡ ሠርቶ ፡ ስሙን ፡ ሊቀድስ ፡ ክብሩን ፡ ሊወርስ ፡ ፈጠረው ፡ ማለት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በርቀት ፡ ፈጠረው ፡ ማለት ፡ አይደለም ። ሰብእሰ ፡ ኢተፈጥረ ፡ ለገዘ ፡ ከመዝ ፡ ከመ ፡ ያጽንኡ ፡ ሃይማኖቶሙ ፡ በረቅ ፡ ወበቀለም ፡ አላ ፡ ይንበሩ ፡ ወይግበሩ ፡ ከመ ፡ መላእክት ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጹሓነ ፡ ወቅዱሳነ ፡ (ኄኖክ) ሕግሰ ፡ ጠባይዓዊ ፡ ተውህበ ፡ ለሰብእ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቀዲሙ ፡ እንዲል ።

፭ ፡ ተፈጥሮውስ ፡ መታመም ፡ መሞት ፡ መፍረስ ፡ መበስበስ ፡ ከሚስማማው ፡ ባሕርይ ፡ ከእሳት ፡ ከነፋስ ፡ ከውሀ ፡ ከመሬት ፡ እንስሳዊ ፡ እውቀትና ፡ እንስሳዊ ፡ ግብር ፡ ያላት ፡ ደማዊት ፡ ነፍስና ፡ መልአካዊ ፡ እውቀት ፡ መልአካዊ ፡ ግብር ፡ ያላት ፡ ነባቢት ፡ ነፍስን ፡ አዋሕዶ ፡ ፈጥሮ ፡ ወአኅጥአ ፡ ሞተ ፡ እንዲል ፡ (መቅድመ ፡ ወንጌል ። )

የማይታመም ፡ የማይሞት ፡ የማይፈርስ ፡ የማይበሰብስ ፡ አድርጎ ፡ ፈጥሮታል ።

፮ ፡ ለነባቢት ፡ ነፍስም ፡ መልአካዊ ፡ እውቀት ፡ መልአካዊ ፡ ግብር ፡ እንዳላት ፡ የሚያስረዳ ፡ ር ፡ መቅድመ ፡ ወንጌልን ፡ የጻፉ ፡ አሞንዮስ ፡ አውሳብዮስ ፡ ሥጋ ፡ ዘፍጹም ፡ ቆሙ ፡ ዘቦቱ ፡ ክልኤቱ ፡ ኃይል ፡ ኃይለ ፡ ዘርዕ ፡ ወኃይለ ፡ እንስሳ ፡ ብለው ፡ ያፀቱ ፡ ባሕርያትንና ፡ የደመ ፡ ነፍስን ፡ ነገር ፡ ከስረዱ ፡ በኋላ ። ወአዲ ፡ አክበሮ ፡ በን



ፍሒት ፡ ዘይእቲ ፡ ማኅተመ ፡ ሕይወት ፡ መንፈሳዊት ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ አክበሮ ፡ እምኵሉ ፡ ፍጥረት ፡ ዘታሕተ ፡ ሰማይ ፡ ወትትኀወቅ ፡ በኃይለ ፡ ንባብ ፡ ወንብረ ፡ ላቲ ፡ ሥልጣነ ፡ በውስቴታ ፡ ትግበር ፡ በከመ ፡ ኀርየት ፡ እንዘ ፡ አልቦ ፡ ዘይኬንና ፡ ወዘይኄይላ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ሠናያቲሃ ፡ ወእከያቲሃ ፡ በሥምረተ ፡ ሕሊናሃ ፡ በአምሳለ ፡ መላእክት ፡ ብለው ፡ ነግረውናል ።

፯ ነባቢት ፡ ነፍስና ፡ ደማዊት ፡ ነፍስም ፡ በፈቃድ ፡ ልዩ ፡ ስለሆኑ ፡ ሥጋን ፡ ለመማረክ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይዋጋሉ ።

፰ እንዲዋጉም ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ በልቡናዬ ፡ ያለ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሕግ ፡ ያማረ ፡ ነበረ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በሰውነቴ ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ሌላ ፡ ሕግ ፡ ኃጢአት ፡ በልቡናዬ ፡ ካለ ፡ ከሕግ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ተዋግቶ ፡ ድል ፡ ነሥቶ ፡ ማረከኝ ፡ እኔ ፡ ደካማ ፡ (ወረዳ) ፡ ነኝ ፡ ከፈራሽ ፡ ከበስባሽ ፡ ሰውነቴ ፡ ማን ፡ ባዳነኝ ፡ ሮሜ ፡ ፯ ፳፬ ፡ ብሏል ።

ሁለተኛም ፡ በፈቃደ ፡ ነፍስ ፡ ጸንታችሁ ፡ ኑሩ ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋችሁን ፡ ግን ፡ አትሥሩ ፡ ሥጋ ፡ ነፍስ ፡ ልትሠራው ፡ የማትወደውን ፡ ይወዳልና ፡ ነፍስም ፡ ሥጋ ፡ ሊሠራው ፡ የማይወደውን ፡ ትወዳለችና ፡ የወደዳችሁትን ፡ እንዳትሠሩ ፡ እስበርሳቸው ፡ ይጣላሉ ፡ ብሏል ፡ ገላ ፡ ም ፡ ፭ ፡ ቍ ፡ ፲፯ ፡ ፲፰ ።

፱ ፡ ደማዊት ፡ ነፍስ ፡ ብታሸንፍ ፡ ሥጋን ፡ ማርካ ፡ ለዲያብሎስ ፡ ታስገዛዋለች ፡ የዲያብሎስን ፡ ፈቃድ ፡ ታስ



www.ethiopianorthodox.org

ፈጽመዋለች ፡ በእንስሳዊ ፡ ግብር ፡ ታኖረዋለች ፡ የእንስሳ ትንም ፡ ሥራ ፡ ታሠራዋለች ።

፲ ፡ የእንስሳትም ፡ ሥራ ፡ ዝሙት ፡ ርኵስ ፡ መዳራት ፡ መጣላት ፡ መኰራት ፡ በሥጋዊ ፡ ነገር ፡ መቃናት ፡ መቈጣት ፡ በሥጋዊ ፡ ነገር ፡ መፈክከር ፡ መጋደል ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ሁሉ ፡ ነው ።

፲፩ ፡ የዲያብሎስንም ፡ ፈቃድ ፡ መፈጸም ፡ አሁን ፡ የቈጠርናቸውን ፡ ሁሉ ፡ መሥራትና ፡ እንስሳት ፡ የማይሠሯቸው ፡ ትርፍ ፡ ነገሮች ፡ ጣዖት ፡ ማምለክ ፡ ወይም ፡ አምልኩኝ ፡ ማለት ፡ ሥር ፡ ምስ ፡ ቅጠል ፡ በጥሶ ፡ ሰውን ፡ በመርዝ ፡ መግደል ፡ በምንዝር ፡ ጌጥ ፡ ማጌጥ ፡ የማይጠረጠረውን ፡ እውነተኛውን ፡ አምላክ ፡ መጠርጠር ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ሁሉ ፡ ነው ፡ ገላ ፡ ም ፡ ፭ ፡ ቊ ፡ ፲፱ ፡ ፳ ፡ ፩ ፡ ፳ ።

፲፪ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ኰናኒተ ፡ ሥጋ ፡ ወኃይሉ ፡ የተባለች ፡ ነባቢት ፡ ነፍስ ፡ ደክማ ፡ ለደማዊት ፡ ነፍስ ፡ ተገዥና ፡ ጥገኛ ፡ ትሆናለች ፡ ሮሜ ፡ ፯ ፡ ቊ ፡ ፱ ፲፩ ፡

፲፫ ፡ ለደማዊት ፡ ነፍስ ፡ ኃይል ፡ የሚሆናትና ፡ ነባቢት ፡ ነፍስን ፡ የሚያደክማትም ፡ በተፈጥሮ ፡ የተሰጠውን ፡ ዕውቀት ፡ በትምርት ፡ ካለማስፋት ፡ የተነሣ ፡ ከጾም ፡ ተከልክሎ ፡ ሲበሉ ፡ ሲጠጡ ፡ ደማዊት ፡ ነፍስ ፡ ኃይል ፡ ታገኛለችና ስለዚህ ፡ ነው ።

፲፬ ፡ ነባቢት ፡ ነፍስም ፡ ብታሸንፍ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ታስገዛዋለች ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ፈቃድ ፡ ታስፈጽመዋለች ፡ መላእክትን ፡ ታስመስለዋለች ፡ በመላእክት ፡ ግብር ፡ ታኖረዋለች ።



፲፭ ፡ የእግዚአብሔርም ፡ ፈቃድ ፡ ፍቅር ፡ ፍሥሐ ፡ ሰላም ፡ ትዕግሥት ፡ ምጽዋት ፡ ኂሩት ፡ ሃይማኖት ፡ የዋሃት ፡ ንጽሕና ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ሁሉ ፡ ነው ፡ ገላ ፡ ፭ ፡ ቊ ፡ ፳፪ ።

፲፮ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ነባቢት ፡ ነፍስ ፡ ኰናኒተ ፡ ሥጋ ፡ ወኃይሉ ፡ ያሰው ፡ ቃል ፡ ተፈጸሞላት ፡ ሥጋን ፡ ደመ ፡ ነፍስን ፡ ትገዛለች ፡ ሮሜ ፡ ም ፡ ፯ ፡ ፳ ፡ ፲ ፡ ፳፬ ።

፲፯ ፡ ለነባቢት ፡ ነፍስም ፡ በሰልፍ ፡ ጊዜ ፡ ኃይል ፡ የሚሰጣትና ፡ የሚረዳት ፡ ጾም ፡ ነው ።

፲፰ ፡ መብል ፡ መጠጥ ፡ ለኃጣውእ ፡ መሠረት ፡ እንደሆኑ ፡ ጾምም ፡ ለትሩፋት ፡ ሁሉ ፡ መሠረት ፡ ነውና ፡ እስመ ፡ ጾም ፡ እማ ፡ ለጸሎት ፡ ወእኅታ ፡ ለአርምሞ ፡ ወነቅዓ ፡ ለአንብዕ ፡ ወጥንተ ፡ ኵሉ ፡ ገድል ፡ ሠናይ ፡ እንዲል ፡ (ማር ፡ ይስ) ፡ አንቀጽ ፡ ፬ ፡ ም ፡ ፯ ፡

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## ለሰው ፡ ሕግ ፡ ስለመሠራቱ ።

፩ ፡ አዳምንም ፡ ትእዛዙን ፡ አፍርሶ ፡ ያልሰጠውን ፡ የባሕርይ ፡ አምላክነቱን ፡ ሲሻ ፡ ቢያገኘው ፡ ከሹመቱ ፡ ሻረው ፡ ከማዕረጉ ፡ አዋረደው ፡ የሞት ፡ ሞት ፡ ፈረደበት ፡ ዘፍ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቊ ፡ ከ፩ ፡ እስከ ፳ ።

፪ አዳምም ፡ ስሕተትን ፡ ከተደረገች ፡ በኋላ ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ ሳትደረግ ፡ አውቆ ፡ የማይሠራት ፡ ከእመቤታችን ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የለምና ፡ ከበደለ ፡ በኋላ ፡ አውቆ ፡ ንስሐ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ቢገባ ፡ ቸርነት ፡ የባሕርዩ ፡ የሚሆን ፡ አምላክ ፡ ፭ሺ ፡ ከ፭፻ ፡ ዘመን ፡ ሲፈጸም ፡ ከልጅ ፡ ልጅህ ፡ ተወልጄ ፡ ሥጋዬን ፡ ቆርሼ ፡ ደሜን ፡ አፍስሼ ፡ አድንሃለሁ ፡ ብሎ ፡ የምሕረት ፡ ተስፋ ፡ ሰጠው ፡ (ቀሌምንጦስ) ፡

፫ ይህም ፡ ተስፋ ፡ ፍጡር ፡ ሁሉ ፡ ምንም ፡ ፍጹም ፡ ኃጢአት ፡ ቢሠራ ፡ አይምረኝም ፡ ብሎ ፡ ተስፋ ፡ ሳይ ቆርጥ ፡ ለቸርነቱ ፡ ምክንያት ፡ የሚሆን ፡ ንስሐ ፡ ከገባ ፡ ፍጹም ፡ ድኅነት ፡ እንዲያገኝ ፡ ያስረዳል ፡ ማቴ ፡ ፲፰ ፡ ፳፩ ፡ ሉቃ ፡ ፲፯ ፡ ፬ ።

፬ ያለንስሐም ፡ ድኅነት ፡ እንዳይገኝ ፡ ከአዳም ፡ አስ ቀድሞ ፡ የበደለ ፡ ዲያብሎስ ፡ ንስሐ ፡ ስላልገባ ፡ ድኅነት ፡ አለማግኘቱ ፡ ያስረዳል ።

፭ አዳምም ፡ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ ለነበረው ፡ ለክርስ ቶስ ፡ ምሳሌው ፡ ስለሆነ ፡ ከሱ ፡ እስከ ፡ ሙሴ ፡ በነ በሩ ፡ ሰዎች ፡ ቢበድሉም ፡ ባይበድሉም ሞት ፡ ተፈ ረደባቸው ፡ ሮሜ ፡ ፭ ፡ ፲፬ ።

፮ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ ለነበረው ፡ ለክርስቶስ ፡ አዳም ፡ ምሳሌው ፡ ነው ፡ ማለትም ፡ በአዳም ፡ ኃጢአት ፡ ዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ እንደተጐዳ ፡ በክርስቶስም ፡ ትሩፋት ፡ ዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ ዳነ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ሮሜ ፡ ፭ ፲፭ ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፭ ፡ ፳፩ ፡ ፳፪ ፡ ፵፭ ።

፯ በሙሴም ፡ ጊዜ ፡ በሕገ ፡ ልቡና ፡ ሊኖር ፡ የተ ፈጠረ ፡ ሰው ፡ በሕገ ፡ ልቡና ፡ መኖር ፡ ተስኖት ፡ በኃ ጢአት ፡ እንደተጐዳ ፡ አውቆ ፡ ለልቡና ፡ አጋዥ ፡ ሊሆን ፡ ሕገ ፡ ኦሪትን ፡ ሠራ ፡ እስመ ፡ ሕገ ፡ ወሀበ ፡ ለረድኤት ፡ እንዲል ፡ ኢሳ ፡ ም ፡ ፰ ፡ ቍ ፡ ፳ ።



፰ ከኦሪት ፡ ጸንተው ፡ የሚኖሩ ፡ ቃላት ፡ አሥር ፡ ናቸው ።

፲ ከነዚህም ፡ መጀመሪያው ፡ ኢታምልክ ፡ ባዕደ ፡ አምላከ ፡ ዘእንበሌየ ።

፪ተኛ ፡ ኢትምሐል ፡ በሐሰት ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጣሪከ ፡

፫ተኛ ፡ ተዘከር ፡ ዕለተ ፡ ሰንበት ።

፬ተኛ ፡ አክብር ፡ አባከ ፡ ወእመከ ።

፭ተኛ ፡ ኢትቅትል ፡ ነፍሰ ።

፮ተኛ ፡ ኢትዘሙ ።

፯ተኛ ፡ ኢትስርቅ ።

፰ተኛ ፡ ኢትኩን ፡ ስምዐ ፡ በሐሰት ።

፱ኛኛ ፡ ኢትፍቱ ።

ዘፀ ፡ ም ፡ ፳ ፡ ቁ ከ፫ድ ፡ እስከ ፡ ፲፰ ፡ ዘዳ ፡ ም ፡ ፭ ፡ ቁ ፡ ከ፯ ፡ እስከ ፡ ፳፱ ፡

፲ ረኛ ፡ አፍቅር ፡ ቢጽከ ፡ ከመ ፡ ነፍስከ ።

ዘሌዋ ፡ ፲፱ ፡ ፲፰ ፡ ቁ ።

፱ ከነዚህም ፡ ፯ቱ ፡ ሕግ ፡ ፫ቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ይባላሉ ።

፲ ፈቃደ ፡ ሥጋና ፡ ፈቃደ ፡ ሰይጣን ፡ ተባብረው ፡ ሥራ ፡ የሠሩ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ ፯ቱን ፡ ትእዛዝ ፤ ፫ቱን ፡ ሕግ ፡ ያስመስሏቸዋል ።

፲፩ በሙሴ ፡ ጊዜ ፡ ተሠሩ ፡ ማለት ፡ በጽሕፈት ፡ ተገ ለጹ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከዚያም ፡ አስቀድሞ ፡



www.ethiopianorthodox.org

በሕገ ፡ ልቡና ፡ ተሠርተው ፡ ቢጠብቋቸው ፡ ዋጋ ፡ ሲያ
ሰጡ ፡ ባይጠብቋቸው ፡ ፍዳ ፡ ሲያመጡ ፡ ኖረዋል ።

፲፱ ፡ ባይጠብቋቸው ፡ ፍዳ ፡ ማምጣታቸው ፡ በምን ፡
ይታወቃል ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ኢታምልክ ፡ ኢት
ስርቅ ፡ ኢትፍቱ ፡ በአዳም ።

ኢትቅትል ፡ ኢትዘሙ ፡ ኢትፍቱ ፡ አፍቅር ፡ ቢጸክ ፡
በቃየል ፡ አስፈርደዋል ።

፳ እንዲያውም ፡ በጠቅላላው ፡ ፲ሩ ፡ ሁሉ ፡ በሰብአ ፡
ትካት ፡ በሰብአ ፡ ሰዶም ፡ በሰብአ ፡ ገሞራ ፡ አስፈርደዋል ።

፳፩ ዋጋ ፡ ማሰጠታቸውም ፡ ኄኖክ ፡ እነሱን ፡ ጠብቆ ፡
በአካል ፡ ሥጋ ፡ ገነት ፡ በመግባቱ ፡ ታውቋል ።

፳፪ ፡ ኖኅም ፡ ያልጠበቋቸው ፡ ሰብአ ፡ ትካት ፡ በማየ ፡
አይኅ ፡ ሲጠፉ ፡ እሱ ፡ ተለይቶ ፡ በመዳኑ ፡ ታውቋል ።

፳፫ ሎጥም ፡ ያልጠበቋቸው ፡ ሰብአ ፡ ሰዶም ፡ ሰብአ ፡
ገሞራ ፡ በእሳት ፡ በጠፉ ፡ ጊዜ ፡ ተለይቶ ፡ በመዳኑ ፡
ታውቋል ።

## ም ዕ ራ ፍ ፫ ።

### ፩ ቃላት ፡ ስለ ፡ ሚፈጸሙበትና ፡ ስለ ፡ ሚፈርሱበት ፡ ምክንያት ።

፩ ከዚህም ፡ ቀጥለን ፡ አሥሩ ፡ ቃላት ፡ የሚፈጸሙበ
ትንና ፡ የሚፈርሱበትን ፡ ምክንያት ፡ እንጽፋለን ።

፪ መጀመሪያው ፡ ሕግ ፡ ኢታምልክ ፡ የሚፈርስ ፡ ጣዖት ፡
በማምለክ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ እግዚአብሔር ፡ ከልፈቀ
ደለት ፡ በሙሴብ ፡ ከቀረበለት ፡ እንጀራ ፡ ጉረሮው ፡ የሚ



ውጠውን ፡ ያህል ፡ ከፍሎ ፡ በጁ ፡ የያዘውን ፡ ለመጉ
ረስ ፡ ከጐረሰውም ፡ በኋላ ፡ እስኪውጠው ፡ ድረስ ፡ በራሱ ፡
ላይ ፡ ሥልጣን ፡ የሌለው ፡ ሰው ፡ ለብዙ ፡ ዘመን ፡ ይሆ
ነኛል ፡ ብሎ ፡ ገንዘብ ፡ በደለበ ፡ ጊዜ ፡ ኢታምልክን ፡
በብዙ ፡ ወገን ፡ ያፈርሳል ።

፫ መጀመሪያ ፡ ዕለተ ፡ ሞትን ረስቶ ፡ ገንዘብ ፡ መሰብ
ሰብ ፡ አልሞትም ፡ ለዘለዓለም ፡ እኖራለሁ ፡ ማለት ፡ ነው ።

፬ አልሞትም ፡ ማለት ፡ ፍጡር ፡ አይደለሁም ፡ ማለት ፡
ነውና ፡ በዚህ ፡ እንዲፈርስ ፡ ይወቅ ።

፭ ገንዘብ ፡ መሰብሰቤ ፡ ለልጆቼ ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡
እኔስ ፡ ለዘለዓለም ፡ እኖራለሁ ፡ ብዬ ፡ አይደለም ፡ የሚል ፡
ሰው ፡ ቢኖር ፡ በራሱ ፡ ሊአገዝ ፡ የማይቻለው ፡ ሰው ፡ ልጆ
ቹን ፡ በኔ ፡ ሥልጣን ፡ አሳድጋለሁ ፡ በኔ ፡ ገንዘብ ፡ እኖ
ራለሁ ፡ ማለት ፡ ቃላቅ ፡ ስሕተት ፡ እንደሆነ ፡ ያስተውል ።

፮ የሚጠፉውንስ ፡ ገንዘብ ፡ ስለሚሰበስብላቸው ፡ ፈንታ ፡
በሕግ ፡ በሥርዓት ፡ ቢያሳድጋቸው ፡ ሌባ ፡ ቀማኛ ፡ የማ
ይወስደውን ፡ ከልሞቱ ፡ የማይጠፋውን ፡ ጥበብን ፡ ቢያስ
ተምራቸው ፡ በተሻለ ፡ ነበር ።

፯ እኔስ ፡ እሞታለሁ ፡ ሲሉ ፡ መኖር ፡ አለና ፡ የተቸገርሁ
ጊዜ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንዳላማርረው ፡ የሰጠኝ ፡ እሱ ፡
እንደሆነ ፡ አውቄ ፡ በገንዘቤ ፡ ከመስረቅ ፡ ከመለመን ፡
ተጠብቄ ፡ እኖራለሁ ፡ እንጅ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አልክ
ድም ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ቢኖር ።

የምቸገርበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ፡ ብሎ ፡ መፍራት ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ መመገብ ፡ የሚቻለው ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ነበር ፡ እንጅ ፡

www.ethiopianorthodox.org

እንግዲህ ፡ ወዲያስ ፡ በዝናም ፡ አብቅሎ ፡ በፀሐይ ፡ አብ
ስሎ ፡ መመገብ ፡ አይቻለውም ፡ ማለቱ ፡ እንደሆነ ፡ ያስ
ተውል ። ማቴ ፡ ፯ ፡ ፳፱ ፡ ሉቃ ፡ ፲፱ ፳፱ ፡ ፴፩ ፡ ፊልጵ ፡
፬ ፯ ፡ ጢሞ ፡ ፯ ፡ ፳ ።

፳ ከሁሉ ፡ በላይ ፡ ልሁን ፡ ማለትም ፡ ጣዖት ፡ ከማም
ለክ ፡ ያደርሳል ፡ ይኸውም ፡ በኢዮርብዓም ፡ ወልደ ፡ ናባጥ ፡
ታውቋል ።

ነገ ፡ ቀ ፡ ፲፪ ፡ ፳፯ ፡ ፳፯ ፡ እስከ ፡ ፴፪ ።

፱ በሐሰት ፡ አትማል ፡ ያለው ፡ ሁለተኛውም ፡ ሕግ ፡
የሚፈርስ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ ወይም ፡ የጻድቃን ፡
የሰማዕታትን ፡ ስም ፡ ጠርቶ ፡ በመማል ፡ ብቻ ፡ አይ
ደለም ።

፲ ሐሰት ፡ከተናገሩ ፡ ሐሰት ፡ ከሰይጣን ፡ የተገኘ ፡ ነውና፡
ሐሰት ፡ በመናገርም ፡ ይፈርሳል ።

፲፩ ፡ ሶስተኛውም ፡ ትእዛዝ ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ሥራህን ፡
ሠርተህ ፡ በ፯ኛው ፡ ሰንበትን ፡ አክብር ፡ ነው ።

፲፪ ፡ በዓልንም ፡ ማክበር ፡ በሥጋ ፡ ላይ ፡ ድካም ፡
ከሚያመጣ ፡ ሥራ ፡ ተከልክሎ ፡ አርፎ ፡ በመዋልና ፡
ሥጋን ፡ ደስ ፡ በማሰኘት ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።

፲፫ ፡ ልቡናን ፡ ከንቱ ፡ ነገር ፡ ከማሰብ ፡ ከልክሎ ፡ የእ
ግዚአብሔርን ፡ ቸርነት ፡ ቢያስቡበት ፡ አንደበትን ፡ ከሐ
ሜት ፡ ከስድብ ፡ ከዋዛ ፡ ከፈዛዛ ፡ ይህን ፡ ከመሰለ ፡
ክፉ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ከልክሎ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ቢያመ
ሰግኑበትና ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ቢናገሩበት ፡ እጅን ፡ የሰ
ውን ፡ ገንዘብ ፡ በግፍ ፡ በመቀማት ፡ ፈንታ ፡ ለመመ



ጽወት ፡ ቢዘረጉት ፡ እግርን ፡ ኃጢአት ፡ ወደ ፡ ሚሰራ
በት ፡ ቦታ ፡ ከመሄድ ፡ ከልክሎ ፡ ወደቤተ ፡ እግዚአ
ብሔርና ፡ ሕሙማንን ፡ ወደመጠየቅ ፡ ቢወስዱት ፡ ነው ፡
እንጂ ፡ ይህ ፡ ካልሆነስ ፡ ከነዚህ ፡ አንዱ ፡ ቢቀር ፡
ሁሉም ፡ ይፈርሳል ።
አምሕርተክሙኒ ፡ ወበዓላቲክሙኒ ፡ ፀልየ ፡ ኢይፈቅድ ፡
ከለው ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ይሆንብናል ፡ ኢሳ ፩ ፲፫ ።

፲፬ አራተኛውም ፡ ትእዛዝ ፡ እናት ፡ አባትህን ፡ አክብር
ነው ።

፲፭ ፡ እናት ፡ አባትንም ፡ ማክበር ፡ ሲመጡ ፡ መቀበል ፡
ሲሄዱ ፡ መሸኘት ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።

ወይም ፡ አባቱ ፡ ከመኳንንቱ ፡ እናቱ ፡ ከወይዛዝሩ ፡ ይበ
ልጣሉ ፡ በማለት ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።

፲፮ ፡ ጉልበታቸው ፡ ሲደክም ፡ ገንዘባቸው ፡ ሲፈጸም ፡
ከብት ፡ ያለው ፡ በከብቱ ፡ ከብት ፡ የሌለው ፡ በጉልበቱ ፡
ወጥቶ ፡ ወርዶ ፡ ቢረዳ ፡ ይፈጸማል ፡ እንጂ ፡ በቃል ፡ አክ
ብሮት ፡ ብቻ ፡ አይፈጸምም ።

፲፯ ፡ አምስተኛውም ፡ ሕግ ፡ ነፍስ ፡ አትግደል ፡ ነው ።

፲፰ ፡ ነፍስ ፡ መግደልም ፡ ጦር ፡ ወርውሮ ፡ በመውጋት ፡
ሰይፍ ፡ መዝ ፡ ጠመንጃ ፡ ተኩሶ ፡ በመምታት ፡ መርዝ ፡
በማጠጣት ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።

፲፱ ፡ ከገዳዮች ፡ ጋራ ፡ ቢመክሩበት ፡ ሲመክሩበትም ፡
ሰምቶ ፡ የሚድንበትን ፡ ምክንያት ፡ ባይሰጡት ።

ገንዘብም ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ በልቶለት ፡ ጠጥቶለት ፡ ከተ
ረፈው ፡ ገንዘቡን ፡ ለነዳያን ፡ አልመጸወተ ፡ ብሎ ፡ ነዳያን
በርሐብ ፡ ቢሞቱ ፡ ነፍስ ፡ ከመግደል ፡ ይቆጠርበታል ።



www.ethiopianorthodox.org

፳ ፡ ካህናትም ፡ ምዕመናንን ፡ እየመከርን ፡ እያስተማርን ፡ መንፈሳዊ ፡ ምግብ ፡ እንመግባቸው ፡ ብለን ፡ ሞተ ፡ ነፍስ ፡ ቢያገኛቸው ፡ በውነት ፡ ነፍስ ፡ መግደል ፡ ማለት ፡ ይህ ፡ ነው ።

፳፩ ፡ ስድስተኛውም ፡ ሕግ ፡ አትሰስን ፡ ነው ።

፳፪ ፡ መሰሰንም ፡ በአባለ ፡ ዘር ፡ ብቻ ፡ ተሠርቶ ፡ የሚቀር ፡ አይደለም ።

፳፫ ፡ ጣዖት ፡ ማምለክ ፡ ከጠንቋይ ፡ ከባለዛር ፡ ሄዶ ፡ መጠየቅ ፡ ዝሙት ፡ ነው ።

፳፬ ፡ ሴት ፡ ዘማ ፡ የምትባል ፡ ከባሏ ፡ አልፋ ፡ ተርፋ ፡ ስትሄድ ፡ እንደሆነ ፡ እነዚህም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አልፈው ከጠንቋይ ፡ ከባለ ፡ ዛር ቢሄዱ ፡ ከዝሙት ፡ ይቆጠርባቸዋል ፡ ወዘመዉ ፡ በጣዖቶሙ ፡ እንዲል ፡ መዝ ፡ ፻፯ ፡ ሕዝ ፡ ፳፫ ፡ ከ፪ ፡ እስከ ፡ ፳፯ ፡ ቁ ።

፳፭ ፡ ያልሰጡትን ፡ መሻት ፡ ያልነገሩትን ፡ ልስማ ፡ ያላሳዩትን ፡ ልይ ፡ ማለትም ፡ ወረት ፡ መውደድ ፡ በልቡና ፡ በዓይን ፡ በገሮ ፡ የሚሰራ ፡ ዝሙት ፡ ነው ።

፳፮ ፡ ሰባተኛ ፡ ሕግ ፡ አትስረቅ ፡ ነው ፡ መስረቅም ፡ አዩኝ ፡ አላዩኝ ፡ ብሎ ፡ የሰው ፡ ገንዘብ ፡ በማንሣሣት ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።

፳፯ ፡ ሊሰማው ፡ ያልተፈቀደለትን ፡ ምሥጢር ፡ ልስማ ፡ ብሎ ፡ መጣጣር ፡ ያንዱን ፡ ነገር ፡ ላንዱ ፡ መንገር ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ከስርቆት ፡ ይቆጠራል ።

፳፰ ፡ ስምንተኛውም ፡ ሕግ ፡ በሐሰት ፡ አትመስክር ፡ ነው ፡ በሐሰት ፡ መመስከርም ፡ እወቅልኝ ፡ ባታውቅብኝ ፡ ባሉት ፡



ጊዜ ፡ ያላየውን ፡ አየሁ ፡ ያልሰማውን ፡ ሰማሁ ፡ ማለት ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።

፳፱ ፡ ጠላቱን ፡ ለመጉዳት ፡ ወይም ፡ ራሱን ፡ ለመጥቀም ፡ ሐሰተኛ ፡ ወሬ ፡ ማውራትም ፡ በሐሰት ፡ መመስከር ፡ ነው ፡ ይኸውም ፡ በ፪ ፡ ረበናት ፡ ታውቋል ፡ ። ዳን ፡ ፲፫ ፡ ፴፱ ።

፴ ፡ ዘጠነኛውም ፡ ሕግ ፡ የባልንጀራህን ፡ ሚስት ፡ የሱም ፡ የሆነውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አትመኝ ፡ ነው ።

፴፩ ፡ ኃጢአት ፡ ሁሉ ፡ በፊቱ ፡ የሚጀመር ፡ ስለሆነ ፡ ኢትፍቱ ፡ ከፈረሰ ፡ እሥሩ ፡ ሁሉ ፡ ይፈርሳሉ ።

፴፪ ፡ የያዘኩት ፡ ይበቃኛል ፡ ማለት ፡ አቅቶት ፡ ያልተሰጠውን ፡ የሚሻ ፡ ሰው ፡ ኃጣውእን ፡ ሁሉ ፡ ፈጽሞ ፡ የያዘውን ፡ ያጣል ።

፴፫ ፡ መሻት ፡ ኢታምልክን ፡ ያስፈርሳል ፡ ይኸውም ፡ በአዳምና ፡ በሔዋን ፡ ታውቋል ።

፴፬ ፡ የተሰጣቸው ፡ የጸጋ ፡ አምላክነት ፡ አንሷቸው ፡ ያልተሰጣቸውን ፡ የባሕርይ ፡ አምላክነት ፡ ባይሹ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡ ባላገኛቸውም ፡ ነበረ ። የያዙትንም ፡ ባላጡት ፡ ነበር ። ዘፍ ፡ ፫ ፡ ካ፩ ፡ እስ ፡ ፯ ።

፴፭ ፡ መሻት ፡ ኢትምሐልን ፡ ያስፈርሳል ፡ ይኸውም ፡ በአይሁድ ፡ ታውቋል ፡ የጌታን ፡ ሞት ፡ ባይሹ ፡ ደሙ ፡ ይኩን ፡ ላዕሌነ ፡ ወላዕለ ፡ ውሉድነ ፡ ብለው ፡ ተማምለው በራሳቸው ፡ ጽኑ ፡ ፍዳ ፡ ባላመጡም ፡ ነበረ ፡ ማቴ ፡ ፳፯ ፡ ፳፭ ።

፴፮ ፡ ፪ተኛም ፡ ቀኖጥራቸው ፡ ከርባ ፡ የሚበዙ ፡ አይሁድ ፡ ጳውሎስን ፡ የመግደል ፡ ፊቱው ፡ ባይነሣሣባቸው ፡

www.ethiopianorthodox.org

ጳውሎስን፡ሰንገደል ፡ እህል ፡ ወሀ ፡ አንቀምስም ፡ ብለው ፡ ባልማሉም ፡ ነበረ ። ግብ ፡ ፳፫ ፡ ፲፪ ።

፴፯ ፡ መሸት ፡ ሰንበትን ፡ ያሸራል ፡ ይኸውም ፡ በሰለጳአድ ፡ ታውቋል ።

፴፰ ፡ የመሥራት ፡ ፈቲው ፡ ስለተነማማበት ፡ ስድስት ፡ ቀን ፡ የሠራው ፡ አንሶት ፡ በሰንበት ፡ እንጨት ፡ ሲሰብር ፡ አግኝቶ ፡ ሙሴ ፡ በደንጋይ ፡ አስወግሮ ፡ ባልገደለውም ፡ ነበረና ። ዘኍል ፡ ፲፭ ፡ ከ፴፪ ፡ እ ፴፯ ።

፴፱ መሸት ፡ አባት ፡ እናት ፡ ማክበርን ፡ ያስፈርሳል ፡ ይኸውም ፡ በአቤሴሎም ፡ ታውቋል ። መንግሥትን ፡ ባይሻ ፡ ባባቱ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ባልሠራም ፡ ነበረና ። መጽ ፡ ሳሙ ፡ ክል ፡ ፲፭ ፡ ፲ ፡ ፲፯ ፡ ፳፩ ፡ ፳፪ ።

፵ ፡ መሸት ፡ ኢትቅትልን ፡ ኢትዘሙን ፡ አፍቅር ፡ ቢጸክን ፡ ያስፈርሳል ። ይኸውም ፡ በቃየልና ፡ በዳዊት ፡ ታውቋል ፡ መሸት ፡ ድል ፡ ባይነሳቸው ፡ ቃየል ፡ አቤልን ባልገደለም ፡ ነበረ ፡ ዘፍ ፡ ፬ ፰ ።

ዳዊትም ፡ በኦርዮ ፡ ላይ ፡ ግፍ ፡ ሠርቶ ፡ ከፈጣሪው ፡ ባልተጣላም ፡ ነበረ ። ፡ መጽ ፡ ሳሙ ፡ ክል ፡ ፲፩ ፡ ፪ ፡ ፬ ፡ ፲፭ ።

፵፩ ፡ መሸት ፡ ኢትስርቅን ፡ ያስፈርሳል ፡ ይኸውም ፡ በአካን ፡ ወልደ ፡ ከርሚ ፡ ታውቋል ።

፵፪ ፡ የገንዘብ ፡ ፈቲው ፡ ባያደርበት ፡ ኢያሱ ፡ ለቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲሆን ፡ ያዘዘውን ፡ ገንዘብ ፡ ሰርቆ ፡ በራሱና ፡ በቤተ ፡ ሰቦቹ ፡ ጥፋት ፡ ባላመጣም ፡ ነበረና ። ዘኢያ ፡ ፯ ፡ ከ ፡ ፩ ፡ እስ ፡ ፳፫ ።



፵፫ ፡ አስረኛውም ፡ ሕግ ፡ ባልንጀራህን ፡ እንደራስህ ፡ አድርገህ ፡ ውደድ ፡ ነው ።

፵፬ ፡ በኢትፍቱ ፡ አሥሩ ፡ ሁሉ ፡ እንደፈረሱ ፡ በአፍቅር ፡ ቢጸክም ፡ ሁሉ ፡ ይፈጸማሉ ። ሮሜ ፡ ፲፫ ፡ ፰ ፡ ፲ ገላ ፡ ፭ ፡ ፲፬ ፡ ጢሞ ፡ ቀ ፡ ፩፭ ።

፵፭ ፡ ወንድሙን ፡ ከወደደው ፡ በሐሰት ፡ አያምለውም ፡ እሱም ፡ አይምልም ።

፵፮ ፡ ወንድሙን ፡ ከወደደው ፡ በሐሰት ፡ አይመሰክርበትም ፡ ከወደደው ፡ አይገድለውም ፡ ከወደደው ፡ አይሰርቀውም ፡ ወንድሙን ፡ ከወደደው ፡ ሚስቱንና ፡ ቤቱን ፡ አይፈልግበትምና ።

፵፯ ፡ ስለዚህ ፡ ኢትፍቱን ፡ የናቀ ፡ አፍቅር ፡ ቢጸክን ፡ የጠበቀ ፡ ሰው ፡ የዲያብሎስ ፡ ጠላት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ወዳጅ ፡ ሆኖ ፡ ይኖራል ።

፵፰ ፡ እኒህን ፡ ፲ሩን ፡ ቃላት ፡ የጠበቁ ፡ ሰዎች በዘመኑ ፡ ብሉይ ፡ ምንም ፡ ከርደተ ፡ ገሃነም ፡ ባይድኑባቸው ፡ በሥጋቸው ፡ ከፀባር ፡ ከቸንፈር ፡ ዳኑባቸው ፡ በነፍሳቸውም ፡ በእደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተጠብቀው ፡ ከሥቃየ ፡ ገሃነም ፡ ዳኑባቸው ። ነፍሰሙሰ ፡ ለጻድቃን ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኢለክፎሙ ፡ ላህበ ፡ ሰቃይ ፡ እንዲል ፡ ጥበብ ፡ ፫ ፩ ።

፵፱ ፡ ፲ሩ ፡ ቃላትንም ፡ ቢጠብቁ ፡ መንፈስ ፡ ረድኤት ፡ አድሮባቸው ፡ የሥጋዊን ፡ ነገር ፡ እየተናገሩ ፡ ምሳሌ ፡ እየመሰሉ ፡ ለአዳም ፡ የነገረውን ፡ ተስፋ ፡ ሲጠባበቁ ፡ ኖሩ ።

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፬ ።

### እመቤታችን ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ስለመግባቷና ፡ ከዚያው ፡ ጌታን ፡ ስለመጽነሷ ።

፩ ፡ ስለ ፡ እመቤታችን ፡ የተነገረው ፡ ትንቢት ፡ የተመሰለው ፡ ምሳሌ ፡ የታወቀ ፡ ስለሆነ ፡ የልደቷን ፡ ነገር ፡ እንናገራለን ።

፪ ፡ የእመቤታችንም ፡ ልደት ፡ ከቤተ ፡ ክህነትና ፡ ከቤተ ፡ መንግሥት ፡ ከተወለዱ ፡ ከሐናና ፡ ከኢያቄም ነው ።

፫ ፡ በተወለደችም ፡ በሦስት ፡ ዓመት ፡ ታኅሣሥ ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ እንደዛሬው ፡ ከቤተ ፡ መቅደስ ፡ አግብተዋታል ።

ይህችንም ፡ ቀን ፡ ተሰብስበን ፡ የምናከብርበት ፡ ስለ ዚህ ፡ ነው ።

፬ ፡ እመቤታችንም ፡ ፲፪ ፡ ዓመት ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ከተቀመጠች ፡ በኋላ ፡ ለአዳም ፡ የነገረው ፡ ቀጠሮ ፡ ቢደርስ ፡ ቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ ወደሷ ፡ ተላከ ፡ ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፳፮ ።

፭ ፡ ተልከም ፡ ወበሳድስ ፡ ወርኅ ፡ ብሎ ፡ ይኩነኒ ፡ እስኪል ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ተነጋገሩ ።

፮ ፡ ለቅዱስ ፡ ገብርኤልም ፡ በመለሰችው ፡ ቃል ፡ ውስጥ ፡ ለኛ ፡ ረብኅ ፡ ጥቅም ፡ የሚሆን ፡ ብዙ ፡ ትምህርት ፡ አስተምራናለች ።

፯ ፡ ከሴቶች ፡ ተለይተሽ ፡ ጸጋን ፡ የተመላሽ ፡ ሆይ ፡ ደስ ፡ ይበልሽ ፡ ቢላት ፡ እናቷ ፡ ሔዋን ፡ ሊያስታት ፡ የመጣ ፡ ሰይጣን ፡ ንባቡን ፡ ደስታ ፡ ምሥጢሩን ፡ መከራ ፡ አድርጎ ፡ የነገራትን ፡ የስሕተት ፡ ቃል ፡ ሳትጠራጠር ፡ በደስታ ፡ ተቀብላ ፡ መከራ ፡ እንዳገኛት ፡ አስባ ፡ እሷን ፡ ያገኝ ፡ እንዳያገኛት ፡ ደንግጣ ፡ በውኑ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ስላምታ ፡ ለሰው ፡ ይገባዋልን ፡ ማለቷ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ትሾማለህ ፡ ትሸለማለህ ፡ ብለው ፡ ሌላም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ የደስታ ፡ ወሬ ፡ በነገሩት ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ከሚለው ፡ ይልቅ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ እውነት ፡ ይሆን ፡ ሐሰት ፤ ለጽድቅን ፡ ይሆን ፡ ለኃጢአት ፡ ለሕይወትን ፡ ይሆን ፡ ለሞት ፡ ብሎ ፡ ማሰብና ፡ መፍራት ፡ እንዲገባ ፡ ያስረዳናል ።



፰ ፡ ሁለተኛም ፡ አምላክን ፡ በድንግልና ፡ ጸንሰሽ ፡ በድንግልና ፡ ትወልጃለሽ ፡ ቢላት ፡ አለወንድ ፡ መውለድ ፡ እንደምን ፡ ይቻላል ፡ ማለቷ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ለማነኛውም ፡ ማዕርግ ፡ ቢሆን ፡ በተመረጠ ፡ ጊዜ ፡ ማዕርጉን ፡ ከመቀበል ፡ አስቀድሞ ፡ የተመረጠበትን ፡ ምክንያት ፡ መርምሮ ፡ ሊያውቅና ፡ ሰውነቱን ፡ ለተመረጠበት ፡ ሥራ ፡ ዝግጁ ፡ ማድረግ ፡ እንዲገባ ፡ ያስረዳናል ።

ሦስተኛም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚሳነው ፡ ነገር ፡ የለምና ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ያድርብሻል ፡ የአብ ፡ ኃይሉ ያጸናሻል ፡ ካንቺ ፡ የሚወለደውም ፡ ከሦስቱ ፡ ቅዱስ ፡ አንዱ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የሚያስረዳ ፡ ነገር ፡ ቢነግራት ። የእግዚአብሔር ፡ ባሪያው ፡ እነሆ ፡ አለሁ ፡ እንደቃልህ ፡ ይደረግልኝ ፡ ማለቷ ። ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሰማውን ፡ ነገር ፡ ከእግዚአብሔር ፡ እንደሆነ ፡ ከተረዳው ፡ በኋላ ። የእግዚአብሔር ፤ ፈቃድ ፡ ይሁንልኝ ፡ ብሎ ፡ በትሕትና ፡ መቀበል ፡ እንዲገባ ፡ ያስረዳናል ።

፲ ፡ ጌታም ፡ ይኩነኒ ፡ ብላ ፡ እስክታምን ፡ ድረስ ቆይቶ ፡ ስታምን ፡ መጸነሱ ፡ ለሰው ፡ የሚሰጥ ፡ በጎ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ያለ ፡ ሃይማኖት ፡ እንዳይፈጽም ፡ ያስረዳናል ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፩ ፡ ይኩነኒ ፡ ስትል ፡ ግን ፡ ቃሏን ፡ ምክንያት ፡ አድርጎ ፡ በማኅፀንዋ ፡ ተቀረጸ ።

፲፪ ፡ ከሁለት ፡ አካል ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ከሁለት ፡ ባሕርይ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ሆነ ፡ በተዋሕዶተ ፡ ቃል ፡ ከበረ ፡ ምንታዌ ፡ ንዴት ፡ ጠፋ ።

፲፫ ፡ ፱ኝ ወር ፡ ከ፭ ፡ ቀን ፡ ሲመላው ፡ ተወለደ ፡ ተወልዶም ፡ የሕፃናትን ፡ ሥራ ፡ እየፈጸመ ፡ አደገ ።



፲፬ ፡ ፴ ፡ ዘመን ፡ ሲመላው ፡ በእደ ፡ ዮሐንስ ፡ በፈለገ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ተጠመቀ ።

፲፭ ፡ ሲጠመቅም ፡ አብ ፡ በሱ ፡ ህልው ፡ ሆኜ ፡ የምመለክበት ፡ የምስገድበት ፡ ልጄ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ መሆኑን ፡ መሰከረ ።



፲፮ ፡ ሁለትነትስ ፡ ቢኖርበት ፡ ዝንቱ ፡ ላንድ ፡ ይነገራል ፡ እንጅ ፡ ለሁለት ፡ አይነገርምና ፡ እነዚህ ፡ ልጆቼ ፡ ናቸው ፡ ባለ ፡ ነበር ፡ እንጅ ፡ ይህ ፡ ልጄ ፡ ነው ፡ ባላለም ፡ ነበር ።

፲፯ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ በዡሪያው ፡ የቆሙት ፡ ሕዝቡ ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ሲል ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ቃል ፡ የተነገረ ፡ ስለ ፡ ዮሐንስ ፡ ነው ፡ ወይንስ ፡ ስለ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ እንዳይጠራጠሩ ፡ በጣት ፡ ጠቅሶ ፡ እንደ ፡ ማሳየት ፡ በርግብ ፡ አምሳል ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ሲቀመጥ ፡ ታይቷል ።

፲፰ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ገዳመ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ገብቶ ፡ ፵ ፡ መዓልት ፡ ፵ ፡ ሌሊት ፡ ጾመ ።

መዋዕለ ፡ ጾሙም ፡ ሲፈጸም ፡ ሊፈታተን ፡ የመጣውን ፡ ሰይጣን ፡ ድል ፡ ነሥቶ ፡ ምድረ ፡ እሥራኤል ፡ ገብቶ ፡ ወንጌልን ፡ አስተማረ ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

<u>፲ሩ ፡ ቃላት ፡ በወንጌል ፡ ስለመጸናታቸው ።</u>

፩ ፡ ሲያስተምርም ፡ አሥሩን ፡ ቃላት ፡ አጸናቸው ፡ እንጅ ፡ አላፈረሳቸውም ። መጀመሪያውን ፡ ትእዛዝ ፡ ኢታምልክን ፡ ማቴ ፡፬ ፡ ፲ ፡ ጽሑፍ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምላክከ ፡ ትሰግድ ፡ ወኪያሁ ፡ ባሕቲቶ ፡ ታምልክ ። አፍቅሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምላክከ ፡ በኵሉ ፡ ልብከ ፡ ወበኵሉ ፡ ነፍስከ ፡ ወበኵሉ ፡ ኃይልከ ፡ ወበኵሉ ፡ ሐሊናከ ፡ ዛቲ ፡ ትእዛዝ ፡ ዐባይ ፡ ወቀዳሚት ፡ ብሎ ፡ አጽንቶታል ፡ ፳፪ ፡ ፴፯ ።

www.ethiopianorthodox.org

፪ ፡ ሁለተኛውንም ፡ ሕግ ፡ ኢትምሐልን ፡ ማቴ ፭ ፡ ፴፫ ፡ በእውነት ፡ እንጅ ፡ በሐሰት ፡ አትማሉ ፡ የተባለውን ፡ ሰምታችኋል ።

እኔ ፡ ግን ፡ እውነቱን ፡ እውነት ፡ ሐሰቱን ፡ ሐሰት ፡ ከማለት ፡ የወጣ ፡ ከሰይጣን ፡ የተገኘ ፡ ነውና ፡ እውነቱን ፡ እውነት ፡ ሐሰቱን ፡ ሐሰት ፡ በሉ ፡ እንጅ ፡ ፈጽማችሁ ፡ አትማሉ ፡ እላችኋለሁ ፡ ብሎ ፡ አጽንቶታል ።

፬ ፡ አራተኛውን ፡ ትእዛዝ ፡ አክብር ፡ አባከ ፡ ወእመከንም ፡ ማቴ ፡ ፲፭ ፡ ፬ ፡ ጸሐፍት ፡ ፈሪሳውያን ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቶችህ ፡ እንጀራ ፡ ሲበሉ ፡ ለምን ፡ እጃቸውን ፡ አይታጠቡም ፡ ቢሉት ፡ እግዚአብሔርስ ፡ እናት ፡ አባታችሁን ፡ አርዱ ፡ እናት ፡ አባቱን ፡ ያልረዳ ፡ የሞት ፡ ሞት ፡ ይሙት ፡ ብሎ ፡ ነበረ ። እናንተ ፡ ግን ፡ ሥራታችሁን ፡ ለማጽናት ፡ እናትና ፡ አባታችሁን ፡ ከኛ ፡ ዩልቅ ፡ አብልጣችሁ ፡ የወደዳችሁት ፡ ገንዘብ ፡ ይርባችሁ ፡ ይጥቀማችሁ ፡ በሏቸው ፡ ብላችሁ ፡ ለልጆች ፡ ለምን ፡ ታስተምራላችሁ? ፡ እናንተ ፡ ግብዞች ፡ ኢሳይያስ ፡ በናንተ እውነት ፡ ነገርን ፡ ተናግሯል ፡ ብሎ ፡ በመገዘፉ ፡ አጽንቶታል ።

፭ ፡ አምስተኛውን ፡ ሕግ ፡ ኢትቅትልን ፡ ማቴ ፡ ፭ ፡ ፳፩ ፡ ፲፭ ፡ ፲፱ ፡ ነፍስ ፡ አትግደሉ ፡ የተባለውን ፡ ሰምታችኋል ።

እኔ ፡ ግን ፡ መግደሉ ፡ ይቅርና ፡ ወንድሙን ፡ ጨርቀ ፡ ለባሽ ፡ አባተ ፡ ታናሽ ፡ ብሎ ፡ የሚያሳዝን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ኃጥእ ፡ ተብሎ ፡ እንዲፈረድበት ፡ እነግራችኋለሁ ፡ ብሎ ፡ አጽንቶታል ።



፮ ፡ ስድስተኛውን ፡ ሕግ ፡ ኢትዘሙንና ፡ ዘጠነኛውን ፡ ሕግ ፡ ኢትፍቱንም ፡ ማቴ ፡ ፭ ፡ ፳፯ ፡ ፲፭ ፡ ፲፱ ፡ አትሰስን ፡ የተባለውን ፡ ሰምታችኋል ።

እኔ ፡ ግን ፡ ሴትን ፡ አይቶ ፡ የወደዳት ፡ ኃጥእ ፡ ተብሎ ፡ ይፈረድበታል ፡ ብሎ ፡ አጽንቷቸዋል ።

፯ ሰባተኛውን ፡ ሕግ ፡ ኢትስርቅንና ፡ ስምንተኛውንም ፡ ሕግ ፡ ኢትኩን ፡ ሰምዓ ፡ በሐሰትን ፡ ማቴ ፡ ፲፭ ፡ ፲፱ ፡ ሰውን ፡ የሚጎዱት ፡ ከልቡና ፡ የሚነቁ ፡ ክፉ ፡ ሐሳቦች ፡ ነፍስ ፡ መግደል ፡ ዝሙት ፡ መስረቅ ፡ በሐሰት ፡ መመስከር ፡ ስድብ ። እሊህ ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ አጽንቷቸዋል ።

፲ አሥረኛውን ፡ ትእዛዝ ፡ አፍቅር ፡ ቢጸከንም ፡ ማቴ ፡ ፭ ፡ ፵፫ ፡ ባልጀራችሁን ፡ ውደዱ ፡ ጠላታችሁን ፡ ጥሉ ፡ የተባለውን ፡ ሰምታችኋል ።

እኔ ፡ ግን ፡ ጠላታችሁን ፡ ውደዱ ፡ እላችኋለሁ ። ወዳጆቻችሁንማ ፡ ብትወዱ ፡ ዋጋችሁ ፡ ምንድንነው ፡ ወዳጆቻቸውንስ ፡ አሕዛብም ፡ ይወዳሉ ፡ ብሎ ፡ አጽንቶታል ።

፲ ሁለተኛም ፡ ፳፪ ፡ ፴፱ ፡ ፍቅረ ፡ እግዚአብሐርን ፡ የምትመስል ፡ የፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሁለተኛ ፡ የምትሆን ፡ ፍቅረ ፡ ቢጽናት ፡ ብሎ ፡ አጽንቶታል ።

፱ ፬ተኛውን ፡ ትእዛዝ ፡ ተዘከር ፡ ዕለተ ፡ ሰንበትንም ፡ ስድስት ፡ ቀን ፡ ዓለምን ፡ ሲፈጥር ፡ ሰንብቶ ፡ ፯ተኛይቱን ፡ ዕለት ፡ ቀዳሚትን ፡ ከሥራ ፡ ዐርፎ ፡ እንዳከበሩት ፡ ሰው ፡ በሆንም ፡ ጊዜ ፡ ፴፫ ፡ ዓመት ፡ ከ፫ ፡ ወር ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሠራውን ፡ የሰውነት ፡ ሥራና ፡ በዕለተ ፡ ዐርብ ፡

www.ethiopianorthodox.org

የተቀበላቸውን ፡ ፲፫ቱን ፡ ሕማማተ ፡ መስቀል ፡ ፈጽሞ ፡ በአካለ ፡ ሥጋ ፡ ስኩብ ፡ በመቃብር ፡ ሆኖ ፡ አርፎበታል ፡ ማቴ ፳፯ ፶፯ ፷፩ ማር ፡ ፲፭ ፡ ፵፪ ፡ ፵፯ ፡ ሉቃ ፡ ፳፫ ፡ ፶፫ ፡ ፶፮ ፡ ዮሐ ፡ ፲፱ ፡ ፵፪ ።



ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መስቀሉን ተሸክሞ ወደ ቀራንዮ ሲሄድ ።


፲ በአካለ ፡ ነፍስም ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ ወርዶ ፡ ፭ሺ ፡ ከ፭፻ ፡ ዘመን ፡ በዲያብሎስ ፡ ቁራኝነት ፡ ተይዘው ፡ የነበሩ ፡ ነፍሳትን ፡ ዓርብ ፡ በሠርክ ፡ አውጥቶ ፡ በገነት ፡ አሳርፎበታል ፡ ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፲፱ ።



## ምዕራፍ ፯ ።

### ከሐዋርያት ፡ በኋላ ፡ የተነሡት ፡ ሊቃውንት ፡ ሥራት ፡ መሥራት ፡ የሚገባቸው ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

፩ ወንጌልንም ፡ ፫ ፡ ዓመት ፡ ከ፫ ፡ ወር ፡ አስተምሮ ፡ ለቤዛ ፡ ዓለም ፡ በማዕከለ ፡ ምድር ፡ ተሰቀለ ፡ ወገብረ ፡ መድኃኒተ ፡ በማዕከለ ፡ ምድር ፡ እንዲል ፡ መዝ ።




በከመ ሰቀልዎ አይሁድ ለእግዚእነ ።

፪ ተሰቅሎም ፡ በሞቱ ፡ ዓለምን ፡ አድኖ ፡ ፫ ፡ መዓልት ፡ ፫ ፡ ሌሊት ፡ በከርሠ ፡ መቃብር ፡ አድሮ ፡ ተነሣ ።

www.ethiopianorthodox.org

፫ ተንሥቶም ፡ ለሐዋርያት ፡ ፵ ፡ ቀን ፡ መጽሐፈ ፡ ኪዳንን ፡ አስተማረ ።

፬ በ፵ ፡ ቀኑም ፡ ሐዋርያትን ፡ ሑሩ ፡ ወመሀሩ ፡ ኵሎ ፡ አሕዛበ ፡ ብሎ ፡ አገዟቸው ፡ዐረገ ።

፭ ባረገም ፡ በ፲ኛው ፡ ቀን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ላከላቸው ፡ እነሱም ፡ በጨለማ ፡ የነገርኳችሁን ፡ በብርሃን ፡ አስተምሩት ።

፮ ቀስ ፡ ብዬ ፡ በጆሩዋችሁ ፡ የነገርኳችሁን ፡ በደባባይ ፡ ገልጻችሁ ፡ አስተምሩት ፡ ማቴ ፡ ፲ ፡ ፳፮ ፡ ቍጥር ።

አብ ፡ በኔ ፡ ስም ፡ የሚልክላችሁ ፡ ጰራቅሊጦስ ፡ ያስተምራችኋል ፡ የነገርኳችሁንም ፡ ሁሉ ፡ ያሳስባችኋል ፡ ብሏቸው ፡ ነበርና ፡ ዮሐንስ ፡ ፲፬ ፡ ፳፮ ፡ ቍጥር ።

በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ታድሰው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እየረዳቸው ፡ ወንጌልን ፡ ለሁሉ ፡ አስተማሩ ፡ ሥርዓተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ሠሩ ።

፯ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በኔ ፡ ስም ፡ አምነው ፡ ሁለት ፡ ወይም ፡ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ ባንድነት ፡ ቢሰበሰቡ ፡ በመካከላቸው ፡ እኖራለሁ ፡ ፲፰ ፡ ፳ ፡ ቍጥር ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ እስኪያልፍ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ከናንተ ፡ ጋራ ፡ እኖራለሁ ፡ ማቴ ፡ ፳፰ ፡ ፳ ፡ ቍጥር ፡ ብሎ ፡ የነገራቸውም ፡ ቃል ፡ በነሱ ፡ ብቻ ፡ የማይወሰን ፡ ሐዋርያትን ፡ መስለው ፡ እስከ ፡ ምጽአት ፡ ለሚነሱ ፡ መምህራን ፡ ሁሉ ፡ የተሰጠ ፡ ሥልጣን ፡ መሆኑን ፡ ስለተረዱት ፡ ሁላችንም ፡ አንድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ተቀብለናልና ፡ ከኛ ፡ የቀረ ፡ ነገር ፡ ቢኖር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በሥርዓት ፡ ጸንታ ፡ ትኖር ፡ ዘንድ ፡



ለሚገባው ፡ ሰው ፡ እግዚአብሔር ፡ ይግለጽለት ፡ ብለው ፡ ከነሱ ፡ ቀጥለው ፡ የሚነሱ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የምትተዳደርበትን ፡ ሥራት ፡ እንዲወስኑ ፡ ፈቀደ ዋል ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ መቅድም ፡ ፳ ፡ ገጽ ።

፰ ከሐዋርያት ፡ በኋላ ፡ በየጊዜው ፡ የተነሡ ፡ ሊቃውንትም ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፈውን ፡ ቃልና ፡ ምእመናንን ፡ በመንገደኛ ፡ አጋንንትን ፡ በወንበዴ ፡ እራሱን ፡ በማምራዊ ፡ መምህራንን ፡ በእንግዳ ፡ ቤት ፡ ጠባቂ ፡ መስሎ ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ ሉቃ ፡ ፲ ፡ ፴ ፡ ሳምራዊ ፡ ለእንግዳ ፡ ቤት ፡ ጠባቂው ፡ ፪ ድሪም ፡ ሰጥቶ ፡ ሽፍቶች ፡ ደብድበው ፡ ጥለውት የሄዱትን ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ አስታመህ ፡ አድንልኝ ፡ ከዚህ ፡ አትርፈህ ፡ ያወጣኸው ፡ ገንዘብ ፡ ቢኖር ፡ እኔ ፡ ስመለስ ፡ እከፍልሃለሁ ፡ አለው ፡ ማለቱ ፡ ሁለት ፡ ድሪም ፡ በብሉይና ፡ በሐዲስ ፡ እየመከራችሁ ፡ እያስተማራችሁ ፡ አጋንንት ፡ እያሳቱ ፡ በነፍስ ፡ ያቆሰሏቸው ፡ ምዕመናንን ፡ አድኑልኝ ማለቱ ፡ እንደሆነ ።

ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ያወጣኸው ፡ ገንዘብ ፡ ፡ ቢኖር ፡ እኔ ፡ ስመለስ ፡ እከፍልሃለሁ ፡ ማለቱ ፡ ከብሉያትና ከሐዲሳት ፡ ሌላ ፡ ድርሰን ፡ ደርሳችሁ ፡ ተግሣጽ ፡ ጽፋችሁ ፡ ያስተማራችሁት ፡ ቢኖር ፡ በምጽአት ፡ ዋጋችሁን ፡ እሰጣችኋለሁ ፡ ማለቱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አስበው ፡ የምንጾምበትንና ፡ የምንበላበትን ፡ የምንሠራበትንና ፡ የምናርፍበትን ፡ ጊዜ ፡ ወስነው ፡ ሠርተውልናል ።

፱ ነገር ፡ ግን ፡ ወየአሥሩ ፡ ያረ ፡ ዓቢየ ፡ ወክቡደ ፡ ወያስክምዎ ፡ ለሰብእ ፡ ዲበ ፡ መትከፍቱ ፡ ወለሊሆ

www.ethiopianorthodox.org

ሙሴ ፡ ኢይለክፍዎ ፡ በአጽባዕቶሙ ፡ እንደ ፡ ተባለ
እንደ ፡ ጸሐፍት ፡ ፈሪሳውያን ፡ ሳይሆን ፡ ማቴ ፡ ፳፫
፬ ፡ ሉቃ ፡ ፲፩ ፡ ፵፮ ፡ እሱ ፡ እራሱ ፡ ሠርቶ ፡ ሥሩ ፡
ያለን ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የሠራውን ፡
ሥራና ፡ ሐዋርያትም ፡ የሠሩትን ፡ ሥራ ፡ መሠረት ፡
አድርገው ፡ ሠርተውልናል ።

ምዕራፍ ፯ ።

## ጾም ፡ በወንጌል ፡ የታዘዘ ፡ ሕግ ፡ ስለመሆኑ ።

፩ የሠሩልንም ፡ ጾም ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ አይደለም ፡
ከጌታ ፡ ከሐዋርያት ፡ የተገኘ ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ ጌታ ፡
ከተጠመቀ ፡ በኋላ ፵ ፡ መዓልት ፡ ፵ ፡ ሌሊት ፡ ጾመ
ማቴ ፡ ፬ ፡ ፩ ፡ ማር ፡ ፩ ፡ ፲፫ ፡ ሉቃ ፡ ፬ ፡ ፩ ።

፪ ጌታችን ፡ መጾሙ ፡ ስለምን ፡ ነው ? ፡ እኛን ፡ ጹሙ ፡
ሲለን ፡ አይደለምን ።

፫ እኛስ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ጌታ ፡ ጾሞልናል ፡ ያው ፡
ይበቃናል ፡ አንጾምም ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ጥምቀ
ቱንም ፡ ጌታ ፡ ተጠምቆልናልና ፡ አንጠመቅም ፡ ማለቱ ፡
እንደሆነ ፡ ያስተውል ።

፬ መዋዕለ ፡ ጾሙም ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ በተራበ ፡
ጊዜ ፡ በሙብል ፡ ምክንያት ፡ ድል ፡ እነሣዋለሁ ፡ ብሎ ፡
የተፈታተነውን ፡ ሰይጣን ፡ በትሕርምት ፡ ድል ፡ ነሥቶታል። ፡

፭ በትሕርምት ፡ ድል ፡ መንሣቱ ፡ ስለምድነው ? በት
ሕርምት ፡ ሆናችሁ ፡ ድል ፡ ንሡ ፡ ሲለን ፡ አይደለምን ።



፮ ለትርነቱ ፡ ምክንያት ፡ የሚሆን ፡ ጥቂት ፡ ሥራ ፡
ሳንሠራ ፡ የርሱ ፡ ድል ፡ መንሣት ፡ ብቻ ፡ የሚበቃንስ ፡
ቢሆን ፡ እኔ ፡ ድል ፡ ነሥቻለሁና ፡ ድል ፡ ንሡ ፡ በላለ
ንም ፡ ነበር ። ዮሐ ፡ ፲፯ ፡ ፴፬ ፡

፯ ሁለተኛም ፡ በስብከቱ ፡ መጀመሪያ ፡ ስለጽድቅ ፡
ብለው ፡ የሚራቡ ፡ የሚጠሙ ፡ ሰዎች ፡ ንዑዳን ፡ ክቡ
ራን ፡ ናቸው ፡ ብሏል ፡ ማቴ ፡ ፭ ፡ ፯ ።

፰ ሦስተኛም ፡ የዮሐንስ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቶች ፡ እኛና
ፈሪሳውያን ፡ እንጾማለን ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቶችህ ፡ ለምን ፡
አይጾሙም ፡ ብለው ፡ ቢጠይቁት ፡ መርዓዊ ፡ እኔ ፡ አብ
ሬያቸው ፡ ሳለሁ ፡ አይጾሙም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እኔ ፡ ከነሱ ፡
የምለይበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ይጾማሉ ፡ አለ ፡
እንጅ ፡ እኔ ፡ ከጾምኩላቸው ፡ አይጾሙም ፡ አላለም ፡ ማቴ ፡
፱ ፡ ፲፬ ፡ ፲፭ ።

፱ እኔ ፡ ሳለሁ አይጾሙም ፡ ማለቱ ፡ ግን ፡ ጌታ ፡ ከል
ሞተና ፡ ካላረገ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አይሰጣቸውም ፡ ዮሐ ፡
፲፯ ፡ ፯ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ካልተሰጣቸው ፡ በመንፈስ ፡
ቅዱስ ፡ ባልታደሰ ፡ ሰውነት ፡ መጾምና ፡ ድል ፡ መንሣት ፡
የማይቻላቸው ፡ ስለሆነ ፡ ነው ፡ ማቴ ፡ ፱ ፡ ፲፬ ።

፲ ይኸውም ፡ ከዚህ ፡ በሚከተለው ፡ የምሳሌ ፡ አነጋ
ገር ፡ ይታወቃል ።

፲፩ ባረጀ ፡ ልብስ ፡ ላይ ፡ አዲስ ፡ ቁራጭ ፡ የሚለ
ጥፍ ፡ የለም ፡ ያዲሱ ፡ ቁራጭ ፡ ኃይል ፡ ቀዳዳውን ፡
ያሰፋዋልና ፡ አዲሱንም ፡ ወይን ፡ ባረጀ ፡ ራዋት ፡ የሚ
ጨምር ፡ የለም ፡ ቢጨምሩትም ፡ ራዋቱ ፡ ይቀደዳል ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወይኑም ፡ ይፈሳል ፡ በአዲስ ፡ ሬዋት ቢጨምሩት ፡ ግን ወይኑ ፡ ሬዋቱን ፡ ያለፋጥል ፡ ሬዋቱም ፡ ወይኑን ፡ ከመ ፍሰስ ፡ ይጠብቀዋል ፡ ማለት ፡ ሐዋርያትን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ባልታደሰ ፡ ሰውነታቸው ፡ ጾም ፡ ጹሙ ፡ የሚላቸው ፡ የለም ። ጹሙ ፡ የሚላቸውም ፡ ቢኖር ፡ ሰውነታቸው ፡ ይጎዳል ፡ ጾሙም ፡ ይፈርሳል ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በታደሰ ፡ ሰውነት ፡ ግን ፡ ቢጾሙ ፡ እነሱ ፡ ጾሙን ፡ ይፈጽሙታል ፡ ጾሙም ፡ እነሱን ፡ ከፈተና ፡ ይጠብቃቸዋል ፡ ማለት ፡ እንደሆነ ፡ ያስረዳል ። ማቴ ፡ ፱ ፡ ፲፯ ፡ ፲፯ ፡ ፲፰ ።

፲፪ ፡ ፬ተኛ ፡ ካልጾሙ ፡ ካልጸለዩም ፡ ሰይጣን ፡ ድል ፡ እንዳይሆን ፡ የሚያስረዳ ፡ ነገር ፡ ሐዋርያት ፡ በማይጾሙበት ፡ ወራት ፡ ጋኔን ፡ ማስወጣት ፡ ተስኗቸው ፡ ነበረና እኛ ፡ ልናስወጣው ፡ ያልተቻለን ፡ ስለምንድን ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ቢጠይቁት ።

ይህ ፡ ሰይጣን ፡ ካልጾሙ ፡ ካልጸለዩ ፡ አይወጣም ፡ ብሎ ፡ የመለሰላቸው ፡ ቃል ፡ ያስረዳል ፡ ማቴ ፡ ፲፯ ፳፩ ፡ ማር ፡ ፱ ፡ ፳፱ ።

፲፫ ፭ተኛ ፡ በመብል ፡ በመጠጥ ፤ ይህንንም ፡ ዓለም ፡ በማሰብ ፡ ልቡናችሁን ፡ እንዳታጸኑ ፡ እወቁ ፡ ወጥመድ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ባሉ ፡ በአዕዋፍ ፡ ድንገት ፡ እንደሚደርስባቸው ፡ ዕለተ ፡ ሞት ፡ ድንገት ፡ ትደርስባችኋለችና ፤ ብሏል ሉቃ ፳፩ ፡ ፴፬ ፡ ፴፮ ።

፲፬ ፡ እንዲሁ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ጾምን ፡ ማስተማሩ ፡ አይደለምን ።



፲፭ ፮ተኛ ፡ በአምላካዊ ፡ ሥራው ፡ ኅብስት ፡ አበርክቶ ፡ ስላበላቸው ፡ የሚሹት ፡ ሰዎች ፡ መምህር ፡ ከዚህ ፡ መቼ ፡ ደረስክ ፡ ብለው ፡ ቢጠይቁት ፡ የምትሹኝ ፡ ኅብስት ፡ አበርክቼ ፡ ስላበላኋችሁ ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ ተአምራቱን ፡ ስላያችሁ ፡ አይደለም ፡ እንግዲህስ ፡ ፃሩ ፡ ጋሩ ፡ ካላቸው ፡ በኋላ ፡ ፃሩ ፡ ጋሩም ፡ ማለቱ ፡ ለዘለዓም ፡ ጸንቶ ፡ ለሚኖር ፡ ለመንፈሳዊ ፡ ምግብ ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ ለኃላፊው ፡ ምግብ ፡ አይደለም ።

ኃላፊውንስ ፡ ምግብ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ አሳልፎታል ፡ አለ ።

፲፮ እንዲህ ፡ ማለት ፡ ብሉ ፡ ጠጡ ፡ ሰውነታችሁን ፡ ተከባከቡ ፡ የምትል ፡ ኦሪትን ፡ አሳለፋት ፡ ማለት ፡ ነው ።

፲፯ ብሉ ፡ ጠጡ ፡ የምትል ፡ ኦሪትን ፡ ካሳለፋት ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ አሕዛብ ፡ ዘመን ፡ ጊዜ ፡ ሳንወስን ፡ ስንበላ ፡ ስንጠጣ ፡ ሥጋችንን ፡ ስንከባከብ ፡ ብንገኝ ፡ ኦሪታውያን ፡ እንዲያሰኘን ፡ ጥርጥር ፡ የለበትም ፡ ዮሐ ፡ ፮ ፡ ፳፯ ።

## ምዕራፍ ፫ ።

### ሊቃውንት ፡ የሠሩትን ፡ ሥራት ፡ መቀበል ፡ እንዲገባ ፡

፩ ሐዋርያትም ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፤ ያለውን ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ አድርገው ፡ ጾመዋል ፡ በአንጾኪያ ፡ ባለች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሆነው ፡ እየጾሙ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሥራ ፡ ሲሠሩ ፡ መንፈስ ፤ ቅዱስ ፡ በርናባስና ፡ ሳውልን ፡ እኔ ፡ ለምወደው ፡ ሥራ ፡ ለዩልኝ ፡ ቢላቸው ፡ ያለፈው ፡ ጾም ፡ ይበቃናል ፡ ሳይሉ ፡ እንደገና ፡ ጾመው ፡ ጸልየው ፡ በአንብሮተ ፡ እድ ፡ ሾመዋቸዋል ።

www.ethiopianorthodox.org

፱ ይኸውም ፡ ፩ጊዜ ፡ ጾም ፡ ይበቃኛል ፡ ማለት ፡ እን
ዳይገባ ፡ መላልሶ ፡ መጾም ፡ እንዲገባ ፡ ያስረዳል ፡ ግብ ፡
፲፫ ፩ ።

፲ ፡ ልስጥራን ፡ ኢቆንዮን ፡ አንጾኪያ ፡ በሚባሉ ፡ ሀገ
ሮች ፡ ያሉ ፡ ምእመናንን ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን በብዙ ፡
ድካም ፡ እንገባት ፡ ዘንድ ፡ አለንና ፡ በሃይማኖት ፡ ጽኑ ፡
ብለው ፡ አስተምረው ቀሳውስትን ፡ መርጠው ፡ ሾመው ፡
ጾም ፡ ጾመው ፡ ጸሎት ፡ ጸልየው ፡ ላመኑበት ፡ ለእግዚአ
ብሔር ፡ አደራ ፡ ሰጥተዋቸው ፡ ኼደዋል ። ግብ ፡ ፲፬
፳፪ ፡ ፳፫ ።

፲፩ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስም ፡ በመብል ፡ ምክንያት ፡ ለተነ
ቃቀፉ ፡ አይሁዳዊና ፡ አረማዊ ፡ ሲጽፍ ፡ አይሁዳዊ ፡ አረ
ማዊን ፡ ይህ ፡ ሁሉን ፡ ባሬ ብሎ ፡ ቢነቅፈው ። በመብል ፡
ምክንያት ፡ ወንድምህን ፡ የምትነቅፈው ፡ ከሆነ ፡ በፍቅር ፡
መሄድህ ፡ ወዴት ፡ አለ ። ክርስቶስ ፡ ስለሱ ፡ የሞተለት ፡
አረማዊ ፡ በመብል ፡ ይጎዳልን ፡ ካለ ፡ በኋላ ። የእግዚአብ
ሔር ፡ መንግሥት ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አምኖ ፡ ጽድቅ ፡
ሰላም ፡ ፍሥሐ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ መብል ፡ መጠጥ ፡ አይ
ደለምና ፡ በደግ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ አትሳደቡ ፡ አለ ።

፲፪ ፡ ሥናይ ፡ የተባለ ፡ መብል ፡ መጠጥ ፡ ነውን ፤ ወይስ ፡
ጾም ፡ ጸሎት ፤ ጾም ፡ ጸሎት ፡ አይደለምን ።

፲፫ ፡ ሥናይ ፡ የተባለስ መብል ፡ መጠጥ ፡ እንዳይደለ ፡
የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት በመብል ፡ በመጠጥ ፡ አይደ
ለም ፡ ያለው ፡ ቃል ፡ ያስረዳል ።



፲፬ ፡ እንደዚህ ፡ በጾም ፡ በጸሎት ፡ ሁኖ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
የሚገዛ ፡ ሰው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የተወደደ ፡ ነው ፡
በሰውም ፡ ዘንድ ፡ የተመረጠ ፡ ነው ።

፲፭ ፡ አሁንም ፡ ወንድሞችን ፡ በበጎ ፡ ምግባር ፡ በሚ
ጸና ፡ ገንዘብ ፡ ፍቅርን ፡ እንሻት ፡ እንጂ ስለ መብል ፡
የእግዚአብሔርን ፡ ሥራ ፡ አንሻር ፡ ብሏል ።

፲፮ ፡ ይህስ ፡ እናንተ ፡ የመጽሐፍ ፡ ስልት ፡ ባታውቁ ፡
ከሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ርኩስ ፡ አለ ፡ ለሚሉ ፡ ሰዎች ፡ የጻ
ፈውን ፡ ለጾም ፡ ሰጥታችሁ ፡ ትናገራላችሁ ፡ እንጂ ፡ እኛስ ፡
በዚሁ ፡ አንቀጽ ፡ በ፪ኛው ፡ ቍጥር ፡ የሚጠራጠር ፡ ሰው ፡
ቅጠል ፡ ይብላ ፡ እንጂ ፡ የሚያምንስ ፡ ሰው ፡ ሁሉን ፡
ሊበላ ፡ ይገባዋል ፡ ብሏል ።

፲፯ በ፳ኛውም ፡ ቍጥር ፡ ሁሉም ፡ ልቡናው ፡ እንዳ
ዘዘው ፡ ይኑር ፡ ብሏል ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ በ፳ ፡ ቍጥር
ለሰው ፡ ክፉ ፡ የሚሆንበት ፡ እየተጠራጠረ ፡ ቢበላ ፡ ነው ፡
እንጂ ፡ ለንጹሕስ ፡ ሁሉ ፡ ንጹሕ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የሥነ፡ ፍጥረ
ትን ፡ ንጹሕነት ፡ ካስረዳ ፡ በኋላ ፡ ሥጋ፡ እየበሉ ፡ ወይን ፡
እየጠጡ ፡ ለወንድም ፡ እንቅፋት ፡ ከመሆን ፤ ሥጋ ፡ አለ
መብላት ፡ ወይን ፡ አለመጠጣት ፡ ይሻላል ፡ ብሏልና ፡ ከመ
ብላት ፡ መጾም ፡ እንዲበልጥ ፡ ይወቅ ።

፲፰ ሁለተኛም ፡ ለጣዖት ፡ የተሠዋውን ፡ በመብ
ላት ፡ ምክንያት ፡ ለተነቃቀፉ ፡ ለቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ፡
ሲጽፍ ፡ ለጣዖት ፡ የተሠዋውን ፡ ስለመብላት ፡ ነገር ፡
የተሠዋላቸው ፡ ጣዖታት ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ከንቱ ፡ እን
ደሆኑ ፡ አምላክም ፡ አንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ እን

www.ethiopianorthodox.org

ደሀን : እናውቃለን : ግን : ይህን : ነገር : ሁሉ : የማያውቀው : አይደለምና : እስከ : ዛሬ : ድረስ : ለጣዖት : የተሠዋውን : የጣዖቱ : ገንዘብ : ነው : እያሉ : በልማድ : የሚበሉ : አሉ ።

የእግዚአብሔር : ገንዘብ : ነው : እንጅ : ለጣዖት : ምን : ገንዘብ : አለው : ሳይሉ : በመብላታቸው : ርኩሳን : ይሆናሉ ፤ ብሎ : ሳያምኑ : የሚበሉትን : ብፁ : ዘልፎ : አል ቀረም ።

፬ : መብላት : በእግዚአብሔር : ዘንድ : ግዳጅ : አይፈጽምልንም : ብንበላ : አንረባም : ባንበላም : አንጐዳምና : አንተ : አማኒው : ከጣዖት : ቤት : ገብተህ : ስትበላ : ዓይቶ : ያ : ተጠራጣሪ : ለጣዖት : የተሠዋውን : በመብላት : ጨኪኖ : እንዳይስት : እወቅ : ብሏል) : እወቅም : ማለቱ : አትብላ : ማለቱ : ነው) : ብትበላ : ግን : ክርስቶ : ስለሱ : የሞተለት : ወንድማችን : አንተን : ዓይቶ : ይጐዳል ።

፭ እንዲህም : እንድርጋችሁ : ወንድማችሁን : ብትበድሉ ፤ ክርስቶስን : መበደላችሁ : ነው ።

እኔስ : በመብል : ምክንያት : ወንድሜ : የሚጐዳ : ከሆነ : ለወንድሜ : መሰናከል : እንዳልሆንበት : ለዘለዓለሙ : ሥጋ : አልበላም : ብሎ ፤ አምኖ : ለሚበላውም : በፊሊጥ : ጾምን : አስተማረው ።

እስመ : ከመዝ : ልማዱ : ለቅዱስ : ጳውሎስ : ያመሠጥር ቃለ : ነገር : እንዲል : ለቅዱስ : ጳውሎስ : ነገር : አራቶ : መናገር : ልማዱ : ነውና : የሐ : አፈ : ፫ኛ : ድር : ፳፰ ገጽ ።

፮ : በማናቸውም : ምክንያት : ቢሆን : ካልበሉ : መቸም መጾማቸው : ነው : ብሎ : ለጣዖት : በተሠዋው : አስጠግቶ : ጾምን : አስተማረ : እንጅ : ለጣዖት : የተሠዋውን አትብሉ : ለማለትስ : በአንጾኪያ : ያሉ : ምእመናንን : ቢጽ : ሐሳዊያን : ገብተው : አምናችሁ : ብትጠመቁ : በሙሴ : ሥርዓት : ካልተገዘራችሁ : አትድኑም : ቢሏቸው : ትምህርት : ተከፍሎብናልሳ : ብለው : ታውከው : ነበርና : እሱንና : በርናባስን : ከተከራከሯቸው በኋላ : ኢየሩሳሌም : ሂዳችሁ : የዚህን : ነገር : ድርሱን : አስታውቁን : ብለው : በላኳቸው : ጊዜ : በኢየሩሳሌም : ሐዋርያትና : ቀሳውስት : ምእመናንም : ሁሉ : አንድ : ሆነው : ከሐዋርያትና : ከቀሳውስት : ከምእመናንም : የተላከች : ክታብ : ከአሕዛብ : ወገን : አምነው : በአንጾኪያ : በሶርያ : በቂልቅያ : ላሉ : ወንድሞቻችን : ትድረስላቸው : ቸር : አላችሁን : ከዚህ : ነገር : አንዱንስ : ስንኳ : ያላዘዝናቸው : ሰዎች : መጥተው : በሙሴ : ሥርዓት : ተገዘሩችሁ : ሕገ : ኦሪትን : ጠብቁ : ብለው : እንዳወኳችሁ : ሰማን : እኛስ : ለጣዖት : የተሠዋውን : ደመ : ነፍስ ያልተለየችውን : በክቱን : ከመብላት : በግድ : ተከልከሉ : እንጅ : ድግ : ተገዘሩ : ብለን : ሥርዓት : አናጸናባችሁም : ብለው : የጻፉትን : ቃል : ቢነግሯቸው : በበቃ : ነበረ : ግብ : ፲፰ : ቍ) : ከንድ : እስከ : ፴ : ቍ ።



www.ethiopianorthodox.org

፯ ከሐዋርያትም ፡ በኋላ ፡ የተነሡ ፡ ሊቃውንት ፡ ይህን ፡ የጌታን፡ የሐዋርያትን ፡ ሥራት ፡ ተከትለው ፡ ሥራ ፡ ቢሠሩ ፡ ልዩ፡ አይባልም ።

፰ ራሱን ፡ በጉንድ ፡ መምህራንን ፡ በአዕፁቅ ፡ መስሎ ፡ ነግሮናል ፡ ዮሐ ፡ ፲፭ ፡ ፩ ፡ የወይን ፡ ተክል ፡ ብዙ ፡ ዐፅቅ ፡ ቢያወጣ ፡ ለመደ ፡ (ፋፋ) ፡ ይባላል ፡ እንጅ ፡ (ዐፅቁ) ፡ ከጉንዱ ፡ ጉንዱ ፡ ከዐፅቁ ፡ ልዩ ፡ ነው ፡ አይባልም ።

፱ ጉንደ ፡ ወይን ፡ ፍሬውን ፡ የሚሰጥ ፡ በአዕፁቅ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ በአዕፁቅ ፡ ላይ ፡ የተገኘ ፡ ፍሬ ፡ የጉንደ ፡ ወይን ፡ ፍሬ ፡ አይደለም ፡ ይባላልን ፡ አይባልም ።

፲ ጌታ ፡ ራሱን ፡ በጉንደ ፡ ወይን ፡ መምህራንን ፡ በአዕፁቅ ፡ መስሎ ፡ ከነገረን ፡ በአዕፁቅ ፡ ከተመሰሉ ፡ ከመምህራን ፡ የተገኘውን ፡ ሥርዓት  አንቀበልም ፡ ማለት ፡ እንደምን ፡ ይቻላል ።

፲፩ (ምሳሌ) ፡ ገበሬ ፡ ዘር ፡ ዘርቶ ፡ አርሞ ፡ ኰትኵቶ ፡ አጭዶ ፡ ወቅቶ ፡ በሪቅ ፡ በጎተራ ፡ ቢከተው ፡ የሚአሰናዳው ፡ ካላገኘ ፡ ሊበላ ፡ አይቻልም ፡ ባለሞያ ፡ ሴት ፡ አበጥራ፡ ፈጭታ፡ አቡክታ ፡ ጋግራ ፡ ያቀረበችው ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ አምሮ ፡ ጣፍጦ ፡ ይበላል ።

፲፪ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ያገበሬ፡አላመረተውም ፡ ይባላልን ? ፡ አይባልም ።

፲፫ እንደዚህም ፡ ሁሉ ፡ ጌታ ፡ እንድንጾም ፡ አዘዘን ፡ እንጅ ፡ የምንጾምበትን ፡ ሰዓት ፡ አልወሰነልንም ።



አነ ፡ እሄሉ ፡ ምስሌክሙ ፡ እስከ ፡ ሕልቀተ ፡ ዓለም ፡ የተባሉ፡ መምህራን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እየተቃኙ ፡ ኀበ ፡ ሀለው ፡ ፪ወ፫ ፡ ጉቡአን ፡ በስምየ ፡ አነ ፡ እሄሉ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ባለው ፡ ቃል ፡ እየረዳቸው ፡ የምንጾምበትን ፡ የምንበላበትን ፡ ሰዓት ፡ ቢወስኑልን ፡ ሥርዓተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ሁሉ ፡ ቢሠሩልን ፡ ከጌታ ፡ ያልተገኘ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ አይገባንም ።

፲፬ ይህንስ ፡ ትተን ፡ ወኵሉ ፡ ዘተጽሕፈ ፡ ለተግሣጽ ፡ ዚአነ ፡ ተጽሕፈ ፡ ከመ ፡ በትዕግሥትነ ፡ ወበተወክሎተ ፡ መጻሕፍት ፡ ንርከብ ፡ ተስፋነ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ተከትለን ፡ ያባቶቻችንን ፡ ሥርዓት ፡ ማጽናት ፡ ይገባናል ፡ ሮሜ ፡ ፲፭ ፬ ።

፲፭ ነገር ፡ ግን ፡ የከበራችሁ ፡ ጌቶችና ፡ ሕዝበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምእመናን ፡ ሆይ ፡ ያለርሱ ፡ ረዳትነት ፡ ምንም ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ አይቻለንምና ፡ አልቦ ፡ ዘይክል ፡ መጺአ ፡ ኀቤየ ፡ እመ ፡ ኢሰሐቦ ፡ አብ ፡ ዘፈነወኒ ፡ ወዘእንበሌየሰ ፡ አልቦ ፡ ዘትክሉ ፡ ገቢረ ፡ ወኢምንተኒ ፡ ያለ ፤ እርሱ ፡ እየረዳን ፡ አባቶቻችንን ፡ ተከትለን ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ እንዲያበቃን ፡ ፀቅን ፡ ልቡና ፡ ሆነን ፡ እንለምነው ።

፲፮ ፡ ትእዛዘ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ካልጠበቁ ፡ የሀገር ፡ ነፃነት ፡ የመንግሥት ፡ ኃይልና ፡ ጽናት ፡ የሕዝብ ፡አንድነት ፡ የሃይማኖት ፡ ስፋት ፡ አይገኝም ፡ ቀድሞ ፡ በሙሴ ፡ ቀጥሎም ፡ በቃሉ ፡ የነገረንን ፡ ትእዛዝና ፡ ሕግ ፡ ብንጠብቅ ፡ ግን ፡ ፍቅርን ፡ ሰላምን ፡ አንድነትን ፡ ገንዘብ ፡ አድርገን ፡

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

በዚህ ፡ ዓለም ፡ ነፃነታችንን ፡ አስከብረን ፡ መንግሥታችንና ፡ ሀገራችንን ፡ አሳፍረን ፡ እንኖራለን ፡ በወዲያኛውም ፡ መንግሥት ፡ ሰማያትን ፡ እንወርሳለን ፡ ብለን ፡ የምናሳስባችሁን ፡ ቃል ፡ አሁን ፡ በኛ ፡ እንደበት ፡ ቢነገር ፡ የጸና ፡ የእግዚአብሔር ፡ አዋጅ ፡ መሆኑን ፡ አውቃችሁ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የጻፍነውን ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ እንድትመለከቱት ፡ እንለምናችኋለን ።

ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ
0911660113
0111/271609
D.N Solomon Yohannes

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org